## 7ኛው የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ቀን በድሬዳዋ ሲከበር አርብቶአደሮች ያስተላለፉት የጋራ አቋም መግለጫ

እኛ የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች በዛሬው ዕለት የ7ኛውን የአርብቶአደር ቀን ስናከብር በጋራ ጉዳዮቻችን ዙሪያ ሠፋ ያለ ውይይት ካደረግን በኋላ ከዚህ በታች ያለውን የጋራ አቋም መግለጫ በማውጣት ለመንግስት አቅርበናል።

1ኛ) የ6ኛውን ዓመት የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ቀን ስናከብር ለመንግስት ያሳለፍናቸው የጋራ አቋም መግለጫ ነጥቦች ማለትም የአርብቶ አደሩ የመንግስት ተቋማዊ አደረጃጀት ከፌደራል እስከ ቀበሌ መዘርጋት፣ የአርብቶ አደሮች የአገር ሽማግሌዎች ምክር ቤት በክልልና በፌደራል ማቋቋም፣ የአርብቶ አደር አካባቢ የብድር ዋስትና አገልግሎት ጥያቄ፣ የአርብቶ አደር አካባቢ ዘላቂ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ የማህበራዊና የመሠረተ ልማት አገልግሎት ማጠናከር እና የአርብቶአደር ቀን ብሔራዊ ቀን እንዲሆን የሚሉት ጥያቄዎቻችን ከሞላ ጐደል ምንም ምላሽ ያልተሠጣቸው በመሆኑ ለእነዚህ ጉዳዮች መንግስት ትኩረት ሠጥቶ በአፋጣኝም ምላሽ እንዲሠጠን አጥብቀን እንጠይቃለን።

2ኛ) የአርብቶአደር አካባቢ የመሬት አጠቃቀም አርብቶ አደሩን ይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግ ፖሊሲ፣ ደንብና መመሪያ ተጠንቶ በአስቸኳይ ተግባራዊ እንዲሆንልን፣

3ኛ) የውሃ ልማት ሥራ የግጦሽ ሀብት ልማትን ከግንዛቤ ያስገባና በአርብቶ አደሩ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲካሄድልን፣

4ኛ) ከተጎራባች የአርብቶአደር ክልሎች ጋር ያለው ግጭት ዘላቂና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ተፈቶ በአካባቢው የሚገኘው የግጦሽና ውሃ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታዎች እንዲመቻቹልን፣

5ኛ) የእንስሳት ጤና አገልግሎት ካለው ተጨባጭ የአርብቶአደር ሁኔታ፣ የእንስሳት ዓይነትና ብዛት ጋር የሚጣጣምበትንና አማራጭ አገልግሎቶች የሚጠናከሩበት መንገድ እንዲመቻችልን፣

6ኛ) የአርብቶአደሩን ማህበረሰብ ያለው የእንስሳት ሀብት፣ ተጠቃሚ ለማድረግ በአገሪቷ ኢኮኖሚ ግንባታ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የገበያ መሠረተ ልማቶች እንዲስፋፉ በመንግስት በኩል ትኩረት እንዲሠጥልን፣

7ኛ) በብሔራዊ ደረጃ በሚሠጠው ፈተና ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚያስገባ ነጥብ እንደሌሎች የአርብቶ አደር ክልሎች የኦሮሚያ አርብቶ አደር አካባቢዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ እንዲመቻችልን፣

8ኛ) በአርብቶ አደር አካባቢዎች የትምህርት አገልግሎት ለማሻሻል የተጀመሩት የአማራጭ ትምህርት ስልቶች በተጓዳኝ የሆስቴል የቦርዲንግ ስኩል አገልግሎት እንዲመቻችልን፣

9ኛ) በአርብቶአደሩ አካባቢ የአርብቶ አደር ልማት ማሠልጠኛ ተቋማት እንዲስፋፉና ሰልጥነው የሚወጡት የልማት ባለሙያዎች በአርብቶ አደሩ የኑሮ ዘይቤና የአካባቢ ሁኔታ ተቃኝተው የሚወጡበት ሁኔታ ይፈጠርልን፣

10ኛ) የአርብቶ አደሩ ባህላዊ የመስተዳደር ተቋማት አቅም የሚገነባበት ከመንግስት የመስተዳደር መዋቅር ጋር በጣምራ በመደጋገፍ የሚሰሩበት ሁኔታ እንዲመቻችልን፣

11ኛ) የ8ኛው የአርብቶ አደሮች ቀን በአገሪቷ ዋና ከተማ በአዲስ አበባ እንዲከበርና በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ በአርብቶ አደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ እና በፓስቶራሊስት ፎረም ኢትዮጵያ በጋራ እንዲያዘጋጅልን፣

12ኛ) በማጠቃለያም ለአርብቶ አደር ማህበረሰብ ኑሮ መሻሻል ሀገራዊ ትኩረት ተሰጥቶ በአገሪቷ የፖለቲካ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ቀጥተኛ ተሳታፊ የሚሆንበት መንገድ እንዲመቻችልን እንጠይቃለን።

ጥር 16 ቀን 1997 ዓ.ም.

<u>ድሬዳዋ</u>